አማኑኤል አለማየሁ (ደጀና)

ሚያዚያ 16/2010

**<u>አላዋቂ ሳሚ ..... (አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና ስርዓቱ)</u>**

አንድ የፖለቲካ ድርጅት የሚከተለውን የፖለቲካ ርእዮት ዓለም አብጠርጥሮ ማወቅ ድርጅቱን ከሚመሩት መሪዎች የሚጠበቅ ነው። ባለፈው "የኢትዮጲያ የፖለቲካ ቀውስ መንስኤና መፍትሄ በእኔ እይታ" በሚል አጠር ያለ ፅሁፌ የኢህአዴግ መሪዎች የሚከተሉትን ፖለቲካዊ ርእዮት ዓለም እንኳን ወደ ህዝብ ሊያስተላልፉት ይቅርና መሪዎችም በቅጡ የያዙት አይመስለኝም ብየ ተከራክሬ ነበር። ይህ የተከራከርኩበት አስተሳሰብ ትክክል ለመሆኑ ማሳያ ሊሆን የሚች በቅርቡ የህውሓት ከፍተኛ አመራሮች ከትግራይ ሙሁራን ጋር ባደረጉት ውይይት በመሰረቱ ትክክል ባልሆነ የፖለቲካ ትርጓሜ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሲተነተን ሰማሁ።

ይህ የተሳሳተ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አተናተንና አተረጓጎም ርእዮት አለሙን ለሚቃወሙት ብቻ ሳይሆን ርእዮት አለሙን ለሚከተሉትንም ጭምር የሚያደናግር በዚህ ደረጃ ባሉ ከፍተኛ አመራሮች ጥርት ያለ ትንታኔና ትርጓሜ መስጠት ካልቻሉ በሌላው ሊፈጠር የሚችውን መዘበራረቅ ለመረዳት የሚያስቸግር አይመስለኝም።

አንድ ርእዮት ዓለም በየወቅቱ እየተገመገመና ጥልቀት እየጨመረ የሚሄድ በዚሁም በምርምርና ስርፀት እየተደገፉ ከወቅቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እዲሁም የማህበረሰብ የባህል ለውጥ ጋር እንዲጣጣም እየተደረገ መሰራት እንዳለበት እሙን ነው። ነገር ግን በመሰረታዊ ርእዮት ዓለሙ በተቀመረበት ወቅት ከሚኖሩ የማህረሰብ ክፍሎች ወይም መደቦች ውስጥ በባለቤትነት ሊያራምዱት በስተመጨረሻም በስርዓት መልክ የሚያንፁትን መደቦች መዘበራረቅም ሆነ አምታቶ ማስቀመጥ የመደብ ትግሉን ከመዘበራረቅ ባለፈም ሊገነባ የሚታሰበውን ስርዓት ባለቤት ሊያሳጣው ይችላል። ከዚህም በዘለለ በግንባታ ሂደቱ ውስጥ የሃይል አሰላለፉን እያዛባ ባለቤት ሆኖ ሊገነባ የሚችለውን የማህበረሰብ ክፍል ራሱን በጥርጣሬ እንዲያይ ብሎም በተቃርኖ እንዲሰለፍ ሊያደርገው ይችላል።

ስለዚህ የአንድ የፖለቲካ ርእዮት ዓለም ባለቤቶቹንና አጋሮቹን ዘበራርቆ ለማስቀመጠ መሞከር አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል እንደሚባለው ይሆንና የሚገነባውን ስርዓት አላስፈላጊ ጥላሸት ይቀባዋል።

በዚህ በትግራይ በተደረገው የህውሓት እና የትግራይ ሙሁራን ስብሰባ (conference) አቶ ስብሓት ነጋ እና ሌሎች አመራሮች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮት አለም ሊገነባው የሚፈልገውን ስርዓት እና ስርዓቱን ለመገንባት የሚሰለፍና የስርዓት መገንባቱ ባለቤት የሆነ መደቦች ሲያብራሩ፡

1. በአብዮታው ዴሞክራሲ ርእዮት አለም የሚገነባው የከበርቴው ስርዓት (capitalist system) እንደሆነ
2. የዚህ የከበርቴው ስርዓት ግንባታ ዋነኛ ተዋናዮችም

2.1 አርሶ አደሩ (the peasant)
2.2 አብዮታዊ ምሁሩ (the revolutionary intellectual)
2.3 ወዝአደሩ (the proletariat)
2.4 ዝቅተኛ ባለሃብት (petty bourgeoisie)

እንደሆነ አብራርተው አስቀምጠዋል።

የአገራች ህዝብ (ህብረተሰብ) በዋናነት ከ80%-90% ከመቶው በአርሶ አደር (peasant) ማህረሰብ የተዋቀረ ነው። ይህ እጅግ በዝቅተኛ የገቢ እና የእውቀት ደረጃ ያለውን ማህበረሰብ በፍጥነትና እና በብዛት ወደ ሌሎች የማህበረሰብ መደቦች ማሸጋገር እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ አብዮታዊ (እመርታዊ) ለውጥ ካልሆነ በዘገምተኛ እና በተለመደው እድገት (conventional growth) ወሳኝ የህብረተብ ክፍሉን ወደ ወዝአደርነት እና ወደ የእድገት መሁር (progressive intellectual) የመቀየር፤ በተጨማሪም በጥንካሬ እና በእውቀት የሚያድገው ክፍሉን ደግሞ ወደ ከበርቴነት የማደግ ሂደቱ አዳጋችና ብዙ አደጋ እስከ አገር ማፍረስ ሊያደርስ የሚያስችል ፈተና ያለበት ነው።

ይህን የማህረሰብ ለውጥ ብሎም የስርዓት እና የስርዓት ምርት ሂደቱን ለመቀየር የሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ብዙ እውነታዎችን (variables) ግምት ውስጥ በማስገባት እና የተስተካከለ ስርዓት እድገት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። የተቀናጀ ስርዓት ትምህርት ማለትም ከመሰረታዊ አካባቢያዊ እውቀት እስከ የከፍተኛ ትምህርት የምርምርና ስርዓት ማእከላት ገንብቶ የአርሶ አደሩን ቁጥር ወደ ሞያተኛ (skilled workforce) እስከ ከፍተኛ ተመራማሪ (scientist) ድረስ እያደረሱ የምሁሩን፣ የወዝ አደሩን እና የባለሃብቱን ቁጥር መጨመር ነው።

በተጨማሪም የገበሬውን ምርታማነት በመጨመርና ከፍተኛ ገቢ እንዲያገኝ በማድረግ እንዲሁም አስፈላጊውን የገበያ ትስስርር ማለትም የአምራች ኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርት ተመጋጋቢነት በመፍጠር ገበሬው ከግብርና ወደ አነስተኛ ብሎም መካከለኛ እያለ የሚያድግ ከግብርና ወደ አምራች ኢንዱስትሪያዊነት የሚሸጋገርበት ስራ መስራት አስፈላጊ ነው።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ርእዮት አለም ዋና አላማው ከስርዓተ ምርቱ ተዋናዮች ውስጥ የገበሬውን መደብ (peasant class) ማቀጨጭና ብሎም ማጥፋት እና ወደ ቀሩት የህብረተሰብ ክፍሎች (መደቦች) ማሸጋገር ነው። በዚህም መሰረት የህብረተሰቡ የመደብ አወቃቀር ከገበሬ መር ወደ ከበርቴው፣ ምሁሩ (መካከለኛው መደብ) እንደዚሁም ወደ ወዛደሩ (blue collar class) በመቀየር ግብርና በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሚና በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ኢኮኖሚው የአገልግሎት እና የአምራች ኢንዱስትሪ የመሪነት ደረጃ ማሳደግ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የስርዓቱ ዋነኛ ባለቤት ማለትም የኢኮኖሚው መዘውር ያዥ ከበርቴው መደብ (the capitalist) ይሆናል ማለት ነው።

የሚገነባው የከበርቴው ስርዓት በተለይም ሙሁሩን እንደ ትልቅ የእውቀት ምንጭ አድርጎ ስለሚጠቀምበት በተቻለ መጠን የምርምርና ስርፀት ተቋማት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ተቋማዊ

አወቃቀሩ የማያቋርጥ የእውቀት ምህዋር ውስጥ ለመቆየት ሲባል የሚደራጅ በመሆኑ እጅግ ከፍተኛ መዋእለንዋይ የሚፈስበት ዘርፍ ስለሚሆን የሙሁራን ሚና የጎላ ይሆናል፡፡

ከመቐለው የሙሁራን ስብሰባ የአቶ ስብሓት ነጋ ማብራሪያ ጋር ሳያይዘው አቶ ስብሓት በማብራሪያቸው ሊከፍሉዋቸው የሞከሩትን ሁለት መደቦች ላይ ላተኩር፡-

1. **መሁሩ**
   በአቶ ስብሓት አገላለፅ በመሪነት የሚሳተፈው "አብዮታዊ ምሁሩ ነው" ይላሉ አብዮታዊ የሚለው የለውጥ ምሁሩ (progressive intellectuals) ለማለት ከሆነ ያስማማናል፡፡ ስለዚህ የአብዮታዊ ምሁርን ትርጓሜ ብዙ ልዮነት በማይፈጥር መንገድ በመውሰድ መለወጥን ማደግን እንደቀዳሚ አጀንዳው አድርጎ በለውጡ ሂደት ላይ የተለየ አቋም ያለው ምሁር ያልታዮ የእድገቱ ገፅታዎችን የማሳየት አቅምን (unseen perspectives of the ideology) ስለሚፈጥር የሚኖረው ሚና እጅግ አስፈላጊና መኖር ያበት የእድገት አጋር ነው፡፡ ምክንያቱም ምርምር እና ስርፁት በእድገት ውስጥ የሚኖራቸው ሚና የሚላከው በአማራጭ መለኪያ (comparison of alternatives) ስለሆነ በዛ ያለ አማራጮች ያሉት የእድገት መንገድ የተሻለ የመምረጥ እድልን ስለሚሰጥ ነው፡፡ ሌላ አማራጭ ለመኖሩ ማወቅ የሚቻለው በመመራመር ነው ፈረንጆች ("there are thousands of ways skinning the goat") እንደሚሉት የምርት እድገት፣ የእውቀት እድገት ወዘተ ብዙ አማራጮች (alternatives) አሉት፡፡ አማራጮቹ ተፈትሸው በምርምር ካላተገኙ በስተቀር በጭፍን ወይም ነብሴ ነገረችኝ ተብሎ የሚኬድ ከሆነ መድረሻው በማይታወቅ መንገድ እንደ መጓዝ ነው፡፡

ለማጠቃለል በምርምር እውቀት በመሰብሰብና በማደራጀት እንዲሁም ምርት እና ምርታማነት በማሳደግ ላይ አይምሯዊ ንብረቱን የሚያፈሰው ምሁር በኔ እይታ የለውጥ ምሁር (progressive intellectual) ነው ባይ ነኝ፡፡ ስለሆነም በዚህ የከበርቴው ስርዓት (capitalist system) ግንባታ የማይተካ ሚና ይጫወታል፡፡

2. **ባለሃብቱ**
   በዚህ በህወሓት አመራሮች አገላለፅ ላይ ያየሁት እና ልዮነት አለኝ ብየ የማየው በባለሃብቱ አተናተን እና አመዳደብ ላይ ነው፡፡
   የአብዮታው ዴሞክራሲ ርእዮት ዓለም ዋና አላማው የከበርቴው ስርዓት መፍጠር ነው፡፡ የከበርቴው ስርዓት ማለት በሚኖረው የሃብት መጠን የተገደበ ከበርቴ መፍጠር ሊሆን አይችም የከበርቴውን የሃብት መጠን ለመገደብ (capital cap) ለማስቀመጥ የሚጥር የስርዓት ግንባታ የኮሚኒስት ስርዓት ግንባታ እንጂ የከበርቴው ስርዓት ግንባታ ሊሆን አይችም፡፡ አቶ ስብሓት በማብራሪቸው ላይ ለመግለፅ የሞከሩት የስርዓት ገንቢዎች አንዱ "ዝቅተኛው ባለሃበት ነው" ያሉት የተሳሳተ ለመሆኑ ከዚህ ቀጥየ ለማስረዳት እሞክራለሁ፡፡

አብዮታው ዴሞክራሲያዊ ርእዮት አለም ለመገንባት የሚፈልገው ስርዓት የከበርቴው ስርዓት ከሆነና የሚገነባው ስርዓት የሃብት ጣርያ (capial cap) የሚያስቀምጥ ከሆነ በዋናነት ሊገነባ የሚፈልገው እጅግ ከፍተናኛ ውድድር በበዛበት ዓለም ውስጥ የኢትዮጲያዊያን ባለሃብቶች በአለም ገበያ የመዳደርና በገበያ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና የተሸለ እየሆነ ዘለቄታዊ የከበርቴው ስርዓት (capitalist system) ገንብቶ የዜጎች የኑሮ ደረጃ በማይዋዥቅ ኢኮኖሚያዊ መሰረት (መደላድል) ላይ ማስቀመጥ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ከፍተኛው ባለሃብት የዚህ የሚገነባው ስርዓት ቀንደኛ ባለቤት እና ያለገደብ ተጠቃሚ ካልሆነ ስርዓቱ የከበርቴው ሊሆን አይችልም ማለት ነው። ምክንያቶም ስርዓቱ አድጎ ጎልብቶ ሊፈጥርም ሊንከባከብም የሚፈልገው የበለፀገ ከበርቴውን ስለሆነ ከበርቴው ዋነኛው ባለቤት ነው። በዋና ባቤትንት የሚተዳደርበትን ስርዓት ሌሎች እዲገነቡለት ሳይሆን በራሱ ሙሉ ተሳትፎ ይገነባዋል እንጂ በዝቅተኛ ባለሃብት ከተገነባ በኋላ ለባለቤትነት የአሰጠጉኝ ልመና ውስጥ ሊገባ አይችልም።

ዝቅተኛው ባለሃብት ወደ መካከለኛ ብሎም ወደ ከፍተኛ ባለሃብትነት በማደግ የስርዓቱ ባለቤት ለመሆን ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ የሚተጋ ሲሆን መካከለኛው ባለሃብት ወደ ከፍተኛ ባለሃብትነት ለማደግ እና የስርዓቱ ቀዳሚ ተጠቃሚ ለመሆን ስለሚሻ በእድገት ሂደቱ ውስጥ ጉልህ ሚና ከሚጫወቱት ውስጥ ናቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ ከህግና ከስርዓት ውጭ ለመበልፀግ የሚሞክሩ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ከህግና ከስርዓት ውጭ ለመበልፀግ የሚሞክሩት፡-

1. የባለሃብቱ መገለጫዎች አይደሉም
2. ከህግና ከስርዓት ውጭ ለመበልፀግ በር የከፈተላቸው ስርዓት የፈለጉትን ያህል ሃብት ቢያከማቹም ሊጠብቃቸውና ዘለቄታዊ ዋስትና ሊሰጣቸው አይችልም። ምክንያቱም እነሱ ለመክበር በሞክሩሩት መንገድ ለመክበር የሚፈልግ ሌላ ጉልበተኛ ተፈጥሮ ህልውናቸውን አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል ስለሆነም የስርዓቱ ጠበቆች ይሆናሉ እንጂ ስርዓቱ ለህገወጥነት ብሎም ለመፍረስ እንዲጋለጥ አያደርጉትም።
3. ከፍተኛው ባለሃብት የሚገነባው ስርዓት የራሱ መሆኑን ስለሚያውቅ ለምርምርና ስርፀት ከፈተኛ ትኩረት በመስጠት ተጨማሪ መዋእለንዋዮን በዚህ ዘርፍ በማዋል አጋዥ ሚና ይጫወታል።
4. በተለይ አሁን እየተፈጠረ ባለው የምርት ሂደቱን በአብዛኛው ወደ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች በመግፋት እና ከፈተኛ መዋእለንዋይ ወደሚጠይቀው የዲዛይን እና እውቀት የማደራጀት ትኩረቱን ስለሚያዞር በአነስተኛ ደረጃ የሚደራጁትን አምራች ተቋማትን የማገዝ ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ የቶዮታ (Toyota) ኩባንያ በስሩ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ አነስኛ እና መለስተኛ አምራቶች እንዳቀፈው ማለት ነው።

ስለዚህ አብዮታው ዴሞክራሲያዊ ርእዮት ዓለም ለሚገነባው የከበርቴው ስርዓት በዋናነት የገንቢነት ሚና የሚጫወቱት :-

1. ዝቅተኛው፣ መካከለኛውም ከፍተኛውም ባለሃብት
2. ወዝአደሩ

3. ሙሁሩ፤ በገንቢነት ሚና ወይንም በመጨመር ላይ መሰረት ያደረገ በመሆኑ
4. አርሶ አደሩ፡- በዚህ በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ርእዮት ዓለም በሚመራው የከበርቴው ስርዓት (capitalist system) ፈጠራ ሂደት ውስጥ የሚኖረው ሚና የራስን መደብ የማጥፋት (self-destruction role) ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ ገበሬው (the peasant) እየቀጨጨና ቁጥሩንና ሚናውን እየቀነሰ ሄዶ የገበሬው መደብ ከላይ ወደገለፁት መሁሩ፣ ወዝአደሩና ከበርቴው መደብ ይቀየርና ይጠፋል።

አርሶ አደሩ፤ በሚገነባው የከበርቴው ስርዓት ባለቤት የሚሆነው የመደብ ለውጥ አድርጎ ራሱን ቀይሮ (transform) አድርጎ እንጂ የገበሬ መደብ ሆኖ አይደለም። አሁን በሄድኩበት አመክንዮ (logic) መሰረት የሚገነባው የከበርቴው ስርዓት የገበሬው ስርዓት አይደለም። የከበርቴው ስርዓት ገበሬውን አያካትትም ስለማይኖር። ስለዚህ የከበርቴው ስርዓት ባለቤቶች ቀሪዎቹ ሶስቱ መደቦች ወዛደሩ፣ ሙሁሩ እና ባለሃቱ ሲሆኑ መሪ ባለቤቱ ደግሞ ባለሃቱ ነው።

በዚህ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርእዮት አለም ውስጥ ከባለቤትነት ባሻገር እጅግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው የመንግስትነት መልኩ (form of the state) ነው፡ ይህ ርእዮት አለም የከበርቴውን ስርዓት ገንብቶ ሙሉ በሙሉ ወደ ባለቤቱ እስኪያስተላልፍ ድረስ አሁን ባለንበት አገራዊም ሆነ አለማቀፋዊ መስፈርቶች (existing variables) መሰረት የሚከተላቸው መርሆዎ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ዲሞክራሲያነት ፡-

   በዚህ የከበርቴው ስርዓት ግንባታ ወቅት ልዮነት እና እነዚህ ልዮነቶች የሚተዳደሩበት ሂደት በዚህ የከበርቴው ስርዓት ግንባታ ሂደት ከወሳኝ ምሰሶዎች አንዱ ነው። በመሆኑም የአሳታፊነት መሰረት ልዮነት ነው።

   ልዮነት በአስሳሰብ፣ ልዮነት በብሄር፣ ልዮነት በፆታ፣ ልዮነት በመደብ፣ እና የመሳሰሉት ልዮነቶች በስርዓት ግንባታው ሂደት በተገቢው እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተግባር ላይና ስጥቶ የመጨመር ሚና (progressive role) እዲኖራቸው ካላደረገ የከበርቴው ስርዓት (capitalist system) ግንባታ ሊሳካ አይችልም። ልዮነትን ለማስተናገድ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መሆን እና ዴሞክራሲዊ ተቋማት መገንባት ግድ ይላል። ዲሞክራሲዊ ሳይሆኑ እና ዴሞክሲያዊ ተቋማት ገንብቶ ግለሰቦችን ከህልውና አስከ አስተሳሰብ ነፃነት (fundamental human and democratic rights) ሊጠበቅ ካልቻለ ዜጎች የሚኖራቸው ሚና ይሁን በመጨረሻ ሊደረስበት የታሰበው የከበርቴው ስርዓት መገንባት አይቻልም።

   ሰዎች መጀመሪያ ጤናቸው ተጠብቆ በሂወት የመኖር መብቸው ለአፍታም ቢሆን ጥያቄ ውስጥ መግባት የለበትም። በሂወት በጤና የሚኖሩ ዜጎች የማሰብ እና የሰስተኛ ወገን መብትን ሳይጋፉ ያሰቡትን የመሆን ህጋዊ እውቅና እና ጥበቃ ሊያገኙ ይገባል። በዚህም መሰረት የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር እና የሚያከብሩና የሚያስከብሩ ተቋማት መገንባት የግድ ነው።

ዜጎች በግል መብታቸው ብቻ ሳይሆን በጋራ የሚይዟቸውን እሴቶቻቸውንም ጭምር ማክበርና ማስከበር ሌላኛው የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ርእዮት አለም መሰረታዊ መርሆ ነው።
ሰዎች ማህበራዊ ፍጡሮች (communal entities) በመሆናችን ምክንያት አካባቢችን (አጠገባችን) ካለው ሰዎ ጋር በመሆን ቋንቋ፣ ባህል፣ ስነልቦና እና አብሮነት እናዳብራለን። ይህ የሚዳብረው አብነት ደግሞ የጋራ እሴታችን ይሆናል። ይህ የጋራ እሴታችን ከምንኖርበት ተፈጥሮአዊ አካባቢ (ecosystem) ጋር በአንድነት የመከበር እና የማስከበር ሙሉ መብት አለን። በተጨማሪም በፆታችን፣ በአስተሳሰባችን፣ በእድሚያችን፣ በሞያችን ወዘተ ተደራጅተን የምናገኘው የወል ማንነት እና የምናከብረው ስርዓት (course of practice) መጠበቅ የሚያስችል ተቋማዊ ጥበቃ እንዲኖር ማድረግ የዚህ የብዝሃት መብና ብዝሃነትን መሰረት ያደረገ አሳታፊነት ሌላኛው ምሰሶ ነው።
ልዮነትን ሊስተናግድና ሊሳትፍ የሚችል ዴሞክራሲዊ ተቋማት እና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያለው ማህበረሰብ ገንብቶ ተቋማዊም ባህላዊም ጥበቃ ለልዮነቶች መስጠት አስፈላጊ ነው።

2. ልማታዊነት (developmentsm)

በተራ ቁጥር አንድ ከገለፅኳቸው አንኳር ነገሮች አንዱ የዜጎች የመኖር መብን ማስከበር የሚያስችል ሰብአዊ መብት መከበር እና ይህንን የሚያረጋግጥ መሆን እንዳለበት ነው። የዜጎች በሂወት የመኖር መብት በድህነት ውስጥ ተሁኖ በቂ ጥበቃ ሊደረግለት አይቻልም። አንድ ዜጋ መሰረታዊ ለመኖር የሚያስፈልገው እንደ ምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ እዲሁም በሂወት እንዲኖር ጥበቃ ሊያደርጉለት የሚገባቸው ተቋማት መገንባት ግድ ይላል።
እነዚህ መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች ለማቅረብ ሆነ ከቀረቡ በኋላም እያዳንዱ ዜጋ ገዝቶ የመጠቀም ዓቅም ማግኘት አለበት። ዜጋ ገዝቶ የመጠቀም ዓቅም ሊያገኝ የሚችው አገሪቱ በዜጎች ላይ መሰረት ያደረገ ወይ ዜጋ ተኮር እድገት ስታመጣ ነው። ዜጋ ተኮር (ሰው ተኮር) እድገት ደግሞ ልማታዊነት ነው። ስለዚህ ዜጎች በሂወት እና መብታቸው ተከብሮ እዲኖሩ በሃገር ደረጃ ልማት ማረጋገጥ አንደኛው የዚህ አብዮታው ዲሞክራሲዊ ርእዮት አለም ምሰሶ ነው።
ስለዚህ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ርእዮት አለም የከበርቴው ስርዓት ለመመስረት (ለመገንባት) አሁን አገራችን ባለችበት ተጨባጭ ሰብአዊና ተፈጥሮአዊ ሃብት፣ አሁን አገራችን ባለችበት መደባዊ እና ህረተሰባዊ ስብጥር መሰረት እንደዚሁም አሁን አለማችን እየተከተለች ባለችበት አለማቀፋዊ የኢኮኖሚ ውህደት (globalism) መሰረት ማድረግ የሚቻለው ልማታዊነትን እና ዴሞክሲዊነትን ሳይነጣጥል በአኩል ሊያስኬድ የሚችል እሳቤ ያለው ስርዓተ መንግስት ማዋቀር ነው። ይህ ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ ስርዓተ መንግስት ከላይ  የተገለፁትን ሁለት መሰረታዊ ተግባራትን ማለትም ዲሞክራሲንና ልማትን የማህበረሰቡ መሰረታዊ (foundation) ማድረግ ከፈለገ ተቋማዊ የማስፈፀም ዓቅም (institutional capacity) እንዲኖረው በቂ ፍኖተ ካርታ (road map) ሊኖረው ይገባል።

3. ተቋማዊ አቅም(institutional capacity)

ሁሉም የተቀደሱ ሃሳቦች ማህበረሰባዊ ለውጥ (positive social impact) ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። የተቀደሱ አስተሳሰቦች የማስፈፀም ዓቅም ባላቸው ተቋማት ከተደገፉና የተስተካከለ ቀልጣፋ (ያልተንዛዛ) አደረጃጀት ከሌላቸው ርቆ እንደተሰቀለ ቋንጣ የሚያስጎመዥ ነገር ግን የማይደርሱ ይሆኑና ዜጎች ከልማቱም ከዲሞክራሲው እንዳየይጠቀሙ በማድረግ ሊገነባ የታሰበው የከበርቴው ስርዓት እንዲጨነግፍ ያደርጋሉ።

በፕሮግራም መልክ የተቀመጡትም ይሁኑ በህግ መልክ የሰፈሩት እሳቤዎች እና መመርያዎች በየቀኑ ጉልበተኞች እየናዷቸው ከግንባታ ይልቅ ወደ አገር መፍረስ ሊያመሩና የከሸፈ አገር (failed state) ሊፈጥር ይችላል።

አብዮታዊ ዲሞክራሲው ርእዮት አለም እሳቤው ለማስፈፀም የሚያስድቀመው መንግስታዊ ቅርፅ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት (democratic developmental state) ተቋማዊ እና ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ዜጎችን የማገልገል ቅንነት ያለው በባህሪው ዴሞክራሲያዊ የሆነ መንግስታዊ መዋቅር (state bureaucracy) የግድ ይለዋል።

ለማጠቃለል የዳበረ የከበርቴው ስርዓት (capitalist system) የመፍጠር ሃላፊነት ለመወጣት የተቀመረው አብዮታዊ ዲሞክራሲዊ ርእዮት አለም፡-

1. አብዮታዊ ነው:- ምክያቱም እመርታዊ ለውጥ (fundamental transformation) ከማምጣቱም በተጨማሪ አርሶ አደርነትን (peasantry) ወደ ወዝአደርነት፣ ወደ ባለሃብትነት እና ወደ ሙሁራዊ ማንነት በገቢ፣ በባህል በሎም በመደብ ስለሚቀይር ነው።
2. ዲሞክራሲያዊ ነው፡- ምክንያቱም የአስተሳሰብ፣ የማንነት፣ የሞያ የገቢ፣ የፆታ እንዲሁም የፖለቲካ ልዮነቶች እውቅና ሰጥቶና አማራጮቹ እንዲኖሩ በጋራ ሰርቶ ማደግን የሚያውቅና የሚያከብር ስርዓት ስለሚገነባ ነው።
3. ልማታዊ ነው፡- ምክንያቱም ሰብአዊና ዴሞክሲያዊ መብቶች ሊሟሉ የሚችሉት ሰዎች (ዜጎች) መልማት ሲችሉ በመሆኑ እና በከፋ ድህነት ውስጥ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማክበር እጅግ አዳጋች ስለሆነ እንዲሁም በዋናነት የሚገነባው ስርዓት መለያው ሃብት ፈጠራ በመሆኑ ልማታዊነት ሌላኛው መሰረታዊ መለያው ነው።

   ከላይ በስፋት ልገልፀው እንደሞከርኩት አብዮታዊ ዲሞክሲያዊ ርእዮት አለም በሶስቱ ገንቢ መደቦች ማለት በምሁሩ፣ በወዛደሩ እና በባለሃብቱ ሙሉ ቁርጠኝነት የሚገነባ ሆኖ አርሶ አደሩ ግን ራሱን ከአርሶ አደርነት (peasantry) ወደ ሌሎች ሶስት መደቦች በመቀየር ሚናው የሚጫወትበት ርእዮት አለም ሲሆን፤ ዴሞክራሲን እና ልማትን ሳይነጣጥል በእኩልነት የሚተገብር መንግስታዊ መዋቀር ፈጥሮ በፍጥነት ወደ ከበርቴው (capitalist system) ስርዓት መሸጋገርን አጥብቆ የሚያምን እሳቤ (ርእዮት) ነው፡፣